የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት
The Benishangul-Gumuz regional state Administrative council

ቁጥር ...............
Ref.
ቀን ....12/8/....2007
Date

ለዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ጽ/ቤት

ጉዳዩ፣ **የፀደቀ መመሪያ ስለመላክ፣**

በዉጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያንና ትውልደ ኢትዮጵያዉያን የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች በክልሉ ከተሞች የምዝገባ ሥርዓት ማስፈጸሚያ ረቂቅ መመሪያ ሚያዚያ 8 ቀን 2007 ዓ/ም በተካሄደዉ የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት /ካቢኔ/ መደበኛ ስብሰባ ላይ በአጀንዳነት ቀርቦ ታይቷል፡፡

በዚሁ መሠረት ካቢኔዉ በቀረበዉ መመሪያ ላይ በጥልቀት ተወያይቶ መመሪያዉን ተቀብሎ አጽቆታል፡፡

ስለዚህ ይኸዉ ታዉቆ መመሪያዉ ሳይዛነፍ በጥንቃቄ ሥራ ላይ እንዲዉል እያሳሰብኩ፣ለአፈጻፀም ያመቺ ዘንድ የፀደቀዉ መመሪያ አንድ ጥራዝ ከዚህ ደበዳቤ ጋር በማያያዝ የተላከ መሆኑን አስታዉቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

አህመድ ናስር
ርእሰ መስተዳድር

<u>እንዲያዉቁት፣</u>

- ለክቡር ም/ር/መስተዳድር/ከአንድ ጥራዝ ጋር/

  <u>በጽ/ቤቱ፣</u>

<u>ግልባጭ፣</u>

- ለከተማ ልማትና ኮንስ/ቢሮ/ከአባሪ ጋር/
- ለሀ/ሥ/ማ/ማ/ማ/ቢሮ / // /

  <u>አሶሳ፣</u>

## መመሪያ ቁጥር ------/2007 ዓ.ም

## በውጭ □ገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች በክልሉ ከተሞች የምዝገባ ሥርዓት ማስፈጸሚያ መመሪያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በተለያዩ ሀገራት የሚኖሩት ኢትዮጵያዉያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን /ዳያስፖራ/ በትውልድ አገራቸው ሁሉ አቀፍ የልማት እንቅስቃሴ ተሣታፊ እንዲሆኑ የሚያስችል የዳያስፖራ ፖሊሲ ቀርፆ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እያደረገ በመሆኑ፤

በፖሊሲው ለአንቀጽ 6.5 (2) እንደተጠቀሰው ዳያስፖራው በግልና በማህበር ተደራጅቶ በክልሎች፣በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች የቁጠባ ሥርዓትን መሠረት ያደረገ የመኖሪያ ቤት ስለሚያገኙበት ሁኔታ በጥናት ላይ የተመሠረተ አሠራር እንደሚዘረጋ በተደነገገው እና በአገር አቀፍ የከተማ ቤት አቅርቦት ስትራቴጂ ማዕቀፍ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በውጭ አገር የሚኖሩ የኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በመኖሪያ ቤት የኅብረት ስራ ማኅበር መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበር የቤት ልማት ኘሮግራም ተጠቃሚ ለመሆን የቤት ፈላጊዎች ምዝገባ በክልሉ ሲካሄድ የምዝገባ ስርዓቱ ወጥነት፣ ግልጽነትና ፍትሃዉነት ባለው መልኩ ለማካሄድ እንዲቻል የአፈጻጸም መመሪያ መውጣት እንዳለበት በመታመኑ፤

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው ክልሉ ህገ-መንግስት እንቀጽ 59 ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት ይህንን የአፈፃፀም መመሪያ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

### አንቀጽ 1

### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በውጭ ሃገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች በክልሉ ከተሞች የምዝገባ ሥርዓት ማስፈጸሚያ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡



22/08 2008 17:10 #0647 P.002/023

**አንቀጽ 2**
**ትርጓሜ**

1) **"ክልል"** ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ክልል ማለት ነው፤
2) **"የኢትዮጵያ ዳያስፖራ"** ማለት ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና የሌላ አገር ዘግነት ያለዉ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ማለት ነው፤
3) **"ሀዋላ"** ማለት በውጭም ሆነ በሀገር ውስጥ በሚገኙ ባንኮች ወይም የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች አማካኝነት ገንዘብ የማዘዋወሪያ ዘዴ ማለት ነው፤
4) **"ዲፕሎማቲክ ፓውች"** ማለት በቪየና ኮንቬንሽን መሰረት ለአንድ ሚሲዮን ኦፊሴላዊ ሥራ ብቻ እንዲያገለግሉ የተፈቀዱ ሠነዶች መያዣና መላላኪያ ከረጢት ማለት ነው፤
5) **"ሚሲዮን"** ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በውጭ ሀገር ያቋቋመው ወይም የሚያቋቁመው ኤምባሲ ወይም ቋሚ መልዕክተኛ ጽህፈት ቤት ወይም ቆንስላ ጽህፈት ቤት ማለት ነው፤
6) **" የመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበር"** ማለት የመኖሪያ ቤት ችግር ያለባቸው ሰዎች የመኖሪያ ቤት ችግራቸውን ለመቅረፍ በጋራ ተሰባስበው በጋራ የሚያቋቁሙትና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚያስተዳድሩት ማህበር ማለት ነዉ፤
7) **"አዲስ የመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበር"** ማለት በማህበር በመደራጀት ቪላ እና አፓርትመንት ቤቶችን ለመገንባት የሚፈልጉ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለመመዝገብ ይህ የምዝገባ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር----/2007" ጸድቆ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በአዲስ መልክ የሚቋቋም የቤት ኅብረት ስራ ማህበር ማለት ነው፤
8) **"በግል ተመዝጋቢ"** ማለት በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በአፓርትመንት ወይም በታውን ሃውስ፣ቪላ በተናጠል ተመዝግቦ በጋራ የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ የሚሆንበት ሥርዓት ማለት ነው፤
9) **"የውክልና ማስረጃ"** ማለት በህግ የተደነገገ ሥርዓትን ተከትሎ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል /ውልና ማስረጃ - Notary Public/ እና ሚሲዮን በአካል ቀርቦ የተሰጠ እና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሆነ በሰነዶች ምዝገባ እና ማረጋገጫ መሥሪያ ቤት የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ማለት ነዉ፤
10) **"ባንክ"** ማለት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማለት ነው፤
11) **"ኢንተርፕራይዝ"** በክልሉ መንግስት ወደፊት የሚቋቋም የቤት ልማት ኢንተርፕራይዝ ማለት ነው፤
12) **"ዲፕሎማት"** ማለት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከሌሎች መንግታስዊ መሥሪያ ቤቶች በኢትዮጵ ፌደራላዊ ዴመክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሚሲዮኖች በውጭ ግንኙነት መስክ ተመድቦ የሚያገለግል ኢትዮጵያዊ ሠራተኛ ማለት ነው፤



Gumuz Regional State Administrative Council

13) **"ሎካል ሠራተኛ"** ማለት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በሌሎች መንግስታዊ መሥሪያ ቤቶች እና በኢትዮጵ ፌደራላዊ ዴመክራሴያዊ ሪፐብሊክ ሚሲዮን ተቀጥሮ በኢትዮጵ ፌደራላዊ ዴመክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሚሲዮን ተመድቦ እያገለገለ የሚገኝ ኢትዮጵያዊ ሠራተኛ (non-diplomatic staff) ማለት ነው፤

14) **"ተመላሽ ዳያስፖራ"** ማለት በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ሀገር ውስጥ ከተመለሱ ከሁለት ዓመት በላይ የቆዩ እና በተለያዩ ስራዎች ተሰማርተው የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ማለት ነው፤

15) **"አደራጅ አካል"** ማለት የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራትን ለማደራጀትና ለመመዝገብ በአዋጅ ስልጣንና ኃላፊነት የተሰጠው የክልሉ ህብረት ስራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ቢሮና በየደረጃው የሚገኙ የህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላትን ያጠቃልላል፤

16) **"አፓርትመንት"** ማለት [redacted]2 እና ከዚያ በላይ ወለል ያላቸው በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ መሠረት የሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ሕንፃዎች ሆነው በጋራ የመኖሪያ ቤት ህግ መሠረት በግል ባለቤትነት የሚያዝ የተሟላ የመኖሪያ ቤት ማለት ነው፤

17) **"ሊዝ"** ማለት በጊዜ በተገደበ ውል መሰረት በከተማ ቦታ የመጠቀም መብት የሚቋቋምበት የመሬት ይዞታ ስሪት ነዉ፤

18) **"የሊዝ መነሻ ዋጋ"** ማለት ዋና ዋና መሰረተ ልማት አዉታሮች ለመዘርጋትም ሆነ ነባር ግንባታዎች በሚገኙበት አከባቢ እነዚህኑ ግንባታዎችና ተያያዥ ንብረተቶች ለማንሳት የሚያስፈልገዉን ወጪ እንዲሁም ለተነሺዎች የሚከፈለዉን ካሳና ሌሎች አግባብነት ያላቸዉን ታሳቢዎች ግምት ዉስጥ ያስገባ የመሬት ሊዝ ዋጋ ማለት ነዉ፤

19) **"ዋና ዋና ከተሞች"** ማለት በክልሉ ዉስጥ የሚገኙ ከፍተኛና መካከለኛ ከተሞችን ያጠቃልላል።

## አንቀጽ 3
## የተፈጻሚነት ወሰን

1) ይህ መመሪያ በመንግስት አስተባባሪነትና ድጋፍ ከሚገነቡት የቤት ልማት ፕሮግራሞች ተጠቃሚ ያልሆኑ በግል ተመዝግበው እና በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ተደራጅተው በክልሉ ከተሞች አፓርትመንት ወይም ቪላ ለመገንባት የሚፈልጉ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ተመላሽ የዲያስፖራ አባላት እንዲሁም በተለያዩ በኢትዮጵ ፌደራላዊ ዴመክራሴያዊ ሪፐብሊክ ሚሲዮኖች ተመድበው/ተቀጥረው በሥራ ላይ የሚገኙ ዲፐሎማቶች እና ሎካል ሰራተኞች አስመልክቶ በክልሉ ዋና ዋና ከተሞች ዉሥጥ ተፈጻሚ ይሆናል፤

2) ይህ መመሪያ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በክልሉ በሚገኙ ከተሞች ለመመዝገብ እንዲችሉ ከክልሉ በጸደቀው መመሪያ መሠረት ምዝገባውና የቦታ ዝግጅቱ ተፈጻሚ ይሆናል።



#0647 P.004/023
22/06 2008 17:11

## አንቀጽ 4

## የመመሪያው ዓላማ

መመሪያዉ የሚከተሉትን ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1) በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በቤት ልማት ፕሮግራሙ ተጠቃሚ ለመሆን ለምዝገባ መስፈርት የሚያስፈልገውን ዝርዝር የአሰራር ሂደት ግልጽ ለማድረግ፤

2) በምዝገባ ሂደት የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት ተቀናጅተው እንዲሰሩ ግልጽ የአሰራር ሥርዓት ለመዘርጋትና ተግባርና ኃላፊነታቸውን አውቀው መመሪያውን እንዲያስፈጽሙ ለማድረግ ነዉ፡፡

## አንቀጽ 5
## መርሆዎች

መመሪያዉ የሚከተሉትን መርሆች ላይ ተመስርቶ ይፈጸማል፡-

1) በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሚካሄዱ የቤት ልማት ፕሮግራሞች ለአገራቸው ብሎም በክልሉ ልማት አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፤

2) ግልጽና ፈጣን የምዝገባ፣ የቁጠባና የአደረጃጀት ሥርዓት በመከተል መረጃዎች ለሁሉም ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል፤

3) ባለድርሻ አካላት በተቀናጀና አሳታፊ በሆነ መልኩ ለጋራ ዓላማ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና ተመላሽ ዳያስፖራ ለመደገፍ መንግስት እያደረገ ያለውን ጥረት እንዲያግዙ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## አንቀጽ 6

## በግል ወይም በመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ በማኅበራት ተደራጅተዉ በቤት መስሪያ ቦታ ፈላጊነት ስለሚያመለክቱ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የመስተንግዶ አግባብ

በውጭ ▯ገር የሚኖሩ ኢትዮኖጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በግል ተመዝግበው ወይም በመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበር ተደራጅተው በቪላ ወይም አፓርትመንት ቤት ለመገንባት ፍላጎት ያላቸው የሚከተሉትን በማሟላት ምዝገባ ማከናወን ይችላሉ፡-

1) እድሜው ከ18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ በህግና በፍርድ ያልተከለከለ ኢትዮጵያዊና ትውልደ ኢትዮጵያዊ፤

2) የጸና የፓስፖርት ቅጂ እና የሚኖሩበት አገር የጸና የመኖሪያ ፈቃድ ወይም የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማኅበር አባልነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፤

3) የሌላ አገር ዜግነት ያገኙ ከሆኑ የጸና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፣

4) የጋብቻ ማስረጃ ዋናውንና ቅጅውን፤

5) ሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶ ግራፍ



22/06 2008 17:11 #0647 P.005/023

6) ለዚሁ ጉዳይ የተዘጋጀ የምዝገባ ቅጽና ውል ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ፤

7) የህብረት ስራ ማኅበር አባልነት መመዝገቢያ ክፍያ መክፈል የሚችል፤

8) ተመዝጋቢዎች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መንግስት በሚያወጣው ፕሮግራም መሠረት የጣት አሻራ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን ይገባቸዋል፤

9) በመረጡት የመኖሪያ ቤት አይነት የግንባታውን ወጪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 11 መሠረት ሙሉ ክፍያ በውጭ ምንዛሪ ከፍለው በአገር ውስጥ በሚከፈተው የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረጉበትን የደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ የሚችሉ፤

10)በመረጡት የቤት አይነት የግንባታውን ወጪ 50 በመቶ ክፍያ በምዝገባ ወቅት በሚኖሩበት አገር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል የባንክ ሂሳብ በመክፈት የሚያስቀምጥና መሬት ተዘጋጅቶ የመኖሪያ ቤት ሥራ ማኅበሩ ሲረከብ የቀሪውን 50 በመቶ ሙሉ በሙሉ በመክፈል የግንባታ ፍቃድ ለመውሰድ ዝግጁ የሆነ እና በውጭ ምንዛሪ ከፍለው በአገር ውስጥ በሚከፈተው የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረጉበትን የደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ የሚችሉ፤

11)ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትዳር ጓደኛው ስም የመኖሪያ ቤትም ሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ በክልሉ ውስጥ በየትኛውም ከተማ የሌለው ወይም ኖሮት ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፤

12) የህብረት ሥራ ማኅበሩን ዓላማና መርሆዎች ለማክበርና የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ለመቀበል ፈቃደኛ የሆነ፤

13) በተለያየ ምክንያት በአካል ቀርበው መመዝገብ የማይችሉ በውጭ ሃገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በግል ተመዝጋቢና በመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበር የሚገነቡ መኖሪያ ቤት ፈላጊዎች በተወካዮቻቸው አማካኝነት የሚከተለውን አሟልተው መመዝገብ ይችላሉ፡-

(ሀ) የወካይ የጸና የፓስፖርት ቅጂ እና ከሚኖሩበት አገር የመኖሪያ ፈቃድ ወይም የኮሚኒቲ ማህበር አባልነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፤

(ለ) ወካይ እና ተወካይ የሌላ አገር ዜግነት ያገኙ ከሆነ የወካይ የጸና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፤

(ሐ) የወካዩ ሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶ ግራፍ፤

(መ) በወካይ ሥም በመረጡት የመኖሪያ ቤት አይነት የግንባታውን ወጪ 50 በመቶ በውጭ ምንዛሪ ከፍለው በአገር ውስጥ በተከፈተው የባንክ አካውንት ገቢ ያደረጉበትን የክፍያ ደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፤

(ሠ) ተወካይ ወካዩን በተመለከተ የተሰጠው መረጃ ስህተት ከሆነ ለመጠየቅ የዝግጁነት ማረጋገጫ ማመልከቻ የሚያቀርብ መሆን አለበት፡፡



#0647 P.006/023
22/06 2008 17:12

15) በመንግስት በተዘረጉት ሌሎች የቤት ልማት ፕሮግራሞች ላይ ተጠቃሚ ያልሆነ ወይም ለመጠቀም ያልተመዘገበ ወይም ተመዝግበም ከሆነ ምዝገባውን መሠረዙን ወይም መተውን ግዴታ መግባት የሚችል አንድ ማህበር በህጋዊ መንገድ በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ለመመዝገብ የሚችለው ሁሉም የማህበሩ አባላት የተገመተውን የግንባታ ወጪ 50 በመቶ መክፈል ሲችሉ ብቻ ነው፤

16) ማህበሩ እንደተመሠረተ የሚቆጠረው የተገመተውን የግንባታውን ወጪ 50 በመቶ ክፍያ ፈጽሞ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፤

17) ሁሉም የኅብረት ሥራ ማኅበራት የራሳቸው መጠሪያ ሲኖራቸው በመጠሪያ ማህበራት ስር ያሉ አባላት በሙሉ የሚቀርብላቸውን ቅጽ 005 በራሳቸው ካልቻሉም በህጋዊ ወኪላቸው አማካኝነት ሙሉ በሙሉ መሙላት ይገባቸዋል፤

18) በክልሉ የሚደራጁ የኅብረት ስራ ማኅበራት የራሳቸውን የግንባታ ዲዛይን በማዘጋጀት ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን ዲዛይኑ እንደ አግባቡ በክልሉ መስተዳድርና ለዚህ ስራ በአዋጅ የተሰጠዉ አካል ሲያጸድቅ ተግባራዊ ይሆናል፤

19) በክልሉ ከተሞች በማኅበር ተደራጅተው የመኖሪያ ቤት ለመስራት ለሚፈልጉ በውጭ ሃገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት የመረጡትን ከተማ ለይተው እንዲያሳውቁና አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት በማድረግ እንዲስተናገዱ ይደረጋል።

## አዘንቀጽ 7

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሚሲዮኖች ተመድበው የሚሰሩ ዲፕሎማቶችና ሎካል ሠራተኞች

1) የመኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ቁጥር 20/2007 ዓ.ም አንቀጽ 7 ላይ የተመለከቱ ሌሎች የአደረጃጀት የምዝገባ መስፈርቶች በተጨማሪ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሚሲዮኖች የሚሰሩ ዲፕሎማቶችና ሎካል ሠራተኞች ፦
   (ሀ) የጸና የኢትዮጵያ ፓስፖርት ቅጂ እና
   (ለ) ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚሰጥ ማረጋገጫ ደብዳቤ አሟልተው ምዝገባ ማከናወን ከፈለጉ በመረጡት የመኖሪያ ቤት አይነት የግንባታ ወጪውን 50 በመቶ በኢትዮጵያ ብር ከፍለው በዳያስፖራው የምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ ተመዝግበው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ለክልሉ ዲያስፖራ ጽህፈት ቤት መላክ አለባቸው።

2) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተዉ የተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ከጸደቀው የመኖሪያ ቤት የህብረት ሥራ ማህበር ቁጥር 20/2007 ዓ.ም አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣ንዑስ አንቀጽ 3፣ንዑስ አንቀጽ 4፣ንዑስ አንቀጽ 6 እና ንዑስ አንቀጽ 7 የተመለከቱት ድንጋጌዎች በዲያስፖራ አባላት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፤

3) በክልሉ ቤት ለመገንባት የሚፈልጉ የማህበራት ዝርዝርና ተፈላጊ ማስረጃዎች ተሟልተው በክልሉ የዲያስፖራ ጽህፈት ቤት ሲቀርብ ምዝገባው በክልሉ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ቢሮ አማካይነት ይሆናል።



22/06 2008 17:12 #0647 P.007/023

## ክፍል ሦስት
## የባንክ ሂሳብ አከፋፈት የሚገነቡ ቤቶች ዓይነት፣ የቦታ ስፋት እና የቤቶች ዋጋ
## አንቀጽ 8
## የባንክ ሂሳብ አከፋፈት

**የባንክ ሂሳብ አከፋፈት፡-**

1) የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለሁሉም የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራትና በግል ተመዝጋቢዎች የሚያገለግል የባንክ ሂሳብ የመክፈት አገልግሎት ብቻ ይሰጣል፤

2) የኅብረት ስራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ቢሮ የጋራ አካውንት (pull account) እንዲከፈት በማድረግ ሁሉም ማኅበራት በእያንዳንዳቸው ሰብሲዲያሪ ሌጀር ተይዞላቸው ከምዝገባው በፊት ወደዚህ ሂሳብ ገቢ እንዲያደርጉ ይደረጋል፤

3) የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገቢ የተደረገውን የእያንዳንዱን ማኅበር የገንዘብ መጠን በተመለከተ ማረጋገጫ ለማኅበራት ማደራጃና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር/ለዲያስፖራ ጽህፈት ቤት ይልካል፤

4) በክልሉ ዉስጥ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እንዲሰጣቸዉ የሚጠይቁ የዲያስፖራ አባላት እንዲገነበላቸዉ የሚፈለጉትን የቤት አይነት የክፍያ መጠን በውጭ ምንዛሪ መክፈል ይኖርባቸዋል፤

5) ተመዝጋቢዎች ክፍያ የሚፈጽሙበት አገሪቱ በምትገበይባቸው ገንዘቦች ብቻ ይሆናል፤

6) ተመዝጋቢዎቹ ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የዳያስፖራ አካውንት ካላቸው ከዚህ ሂሳብ ወደ መኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ሂሳብ እንዲዞርላቸው ማድረግ ይችላሉ፤

7) በውጭ □ገር የሚኖሩ በግል ተመዝጋቢዎችና በማኅበር የተደራጁ የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች የምዝገባና የባንክ ሂሳብ የመክፈት ሂደቱን ለማስፈጸም ማሟላት የሚጠበቅባቸው መሥፈርቶች፡-

(ሀ) የጸና የፓስፖርት ቅጂ እና ከሚኖሩበት አገር የመኖሪያ ፈቃድ ወይም የኮሚኒቲ ማህበር አባልነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፤

(ለ) የሌላ አገር ዜግነት ያገኙ ከሆነ የጸና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፤

(ሐ) *ሁለት* ፓስፖርት መጠን ፎቶ ግራፍ፤

(መ) ለዚህ ጉዳይ የተዘጋጀውን የምዝገባ ቅጽና ውል ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ፤

(ሠ) በመረጡት የመኖሪያ ቤት አይነት የግንባታውን ወጪ 50 በመቶ በውጭ ምንዛሪ በመላክ በአገር ውስጥ በሚከፈተው የባንክ አካውንት ገቢ ያደረጉበትን የክፍያ ደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

9) በአገር ውስጥ በተለያዩ የኢንቨስትመንት፣ የንግድና የሙያ ሥራ ዘርፎች የተሰማሩና አገር ውስጥ ሁለት ዓመት እና ከዚያ በላይ እየኖሩ ያሉ ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት የሚከተሉትን ሲያሟሉ ብቻ በኢትዮጵያ ብር ከፍለው ሂሳብ መክፈት ይችላሉ፡፡



Gurage Regional State Administrative Council

22/06 2008 17:13 #0647 P.008/023

(ሀ) ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የሆኑ ተመላሽ የዳያስፖራ አባላትን በተመለከተ፤

1. የጸና ፓስፖርት ዋናውንና ቅጂውን፤
2. የውጭ ዜግነት ያለው ከሆነ የጸና የትውልደ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ ዋናውንና ቅጂውን፤
3. አገር ውስጥ ቢያንስ ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማቅረብ፤
4. በአገር ውስጥ በአለም አቀፍ /አህጉራዊ ድርጅቶች፣ በመንግስታዊ፣ መንግስታዊ ባልሆኑ እና በግል ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥሮ የሚሠራና ወርሀዊ ክፍያው በኢትዮጵያ ብር እንደሆነና ግብር ከፋይ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማቅረብ የሚችል፤
5. በአገር ውስጥ ሌላ የመተዳደሪያ ገቢ ካለው ይህንኑ የሚገልጽ ማስረጃ ዋናውንና ቅጂውን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

(ለ) ኢትዮጵያዊያን የሆኑ ተመላሽ የዳያስፖራ አባላትን በተመለከተ፡-

1. የጸና ፓስፖርት ዋናውንና ቅጂውን፤
2. ከኖረበት አገር የጸና የመኖሪያ ፈቃድ ዋናውንና ቅጂውን፤
3. አገር ውስጥ ከሁለት ዓመት በላይ ያለመኖሩን/ሯን የሚያሳይ ማስረጃ ዋናውንና ቅጂውን ወይም፤
4. በአገር ውስጥ በአለም አቀፍ /አህጉራዊ ድርጅቶች፣ በመንግስታዊ፣ መንግስታዊ ባልሆኑ እና በግል ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥሮ የሚሠራና ወርሀዊ ክፍያው በኢትዮጵያ ብር እንደሆነና ግብር ከፋይ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## <u>አንቀጽ 9</u>

## <u>የሚገነቡ ቤቶች ዓይነት፣ የቦታ ስፋት እና የቤቶች ዋጋ</u>

1) በውጭ አገር በሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በግል ተመዝጋቢና ወይም የመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበራት የሚገነቡት መኖሪያ ቤቶች በክልሉ ከተሞች አፓርትመንት እና ቪላ ሲሆኑ የቤቶቹ ስፋት እና ጠቅላላ ዋጋ ለመነሻነት እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ሀ) በክልሉ ዋና ዋና ከተሞች በአፓርትመንት (G+2 እና በላይ) አማራጭ

1. ባለ 2 መኝታ የቤቱ ስፋት 74 ካ.ሜ. ሲሆን ዋጋው ብር 424,390 ነው፤
2. ባለ 3 መኝታ የቤቱ ስፋት 100 ካ.ሜ. ሲሆን ዋጋው ብር 573,500 ነው፤
3. ባለ 4 መኝታ የቤቱ ስፋት 136 ካ.ሜ. ሲሆን ዋጋው ብር 779,960 ነው፡፡

ለ) በክልሉ ዋና ዋና ከተሞች በቪላ (G+1 እና በላይ) አማራጭ



#0647 P.009/023
22/06 2008 17:13

1. ባለ 3 መኝታ የቤቱ ስፋት 114 ካ.ሜ. ሲሆን ዋጋው ብር 693,120 ነው፤

2. ባለ 4 መኝታ የቤቱ ስፋት 150 ካ.ሜ. ሲሆን ዋጋው ብር 912,000 ነው።

2) ከላይ የተጠቀሱት የግንባታ ዋጋዎች በአሁኑ ወቅት ባልታዩ አሳማኝ በሆኑ ምክንያቶኛ የዋጋ ልዩነት ሊኖር ይችላል፤

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 "ሀ" እና "ለ" የተጠቀሰዉ የግንባታ መነሻ ዋጋ ሲሆን እንደ አካባቢዉ ሁኔታ ሊለዋወጥ እንደሚችል ታሳቢ መደረግ አለበት፤

4) የዲዛይኑን ዓይነት በራሳቸው መርጠው ለሚያሰሩ የቤቱ ግንባታ ዋጋ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ሊሆን አይችልም፤ሆኖም ማኅበሩ የሚያቀርበውን ዲዛይን መሠረት በማድረግ የሚመለከተው አካል በሚገምተው የግንባታ ዋጋ ይሆናል። ነገር ግን ዲዛይኑ በከተማዉ ስታንዳርድ ሁኖ በሚመለከተዉ አካል ተቀባይነት ሲያገኝ ነዉ፤

5) ቦታ የሚሰጠዉ በሊዝ መነሻ ዋጋ ይሆናል፤

6) ከአራት በላይ የሆኑ ማኅበራት (48 እና ከዚያ በላይ አባላት) በዩኒየን ተደራጅተው High rise ህንፃ በመሃል ከተማ መገንባት ከፈለጉ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እንዲገነቡ የሚፈቀድላቸው ይሆናል።

## ክፍል አራት
## የባለድርሻ አካለት ተግባርና ኃላፊነት
## አንቀጽ 10

**1. የክልሉ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት**

(ሀ) ለኢትዮጵያ ዲያስፖራ በመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበርና በግል ተመዝጋቢዎች የተቀናጀ አሰራር እንዲከተሉ የሚያግዝ ማስፈጸሚያ መመሪያ በማዘጋጀት ስለ አፈጻጸሙ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

(ለ) ከከተሞችና ከሚመለከተዉ አካል ጋር በመሆን የመሰረተ ልማት አቅርቦት እንዲኖር ማስቻል፣ ስታንዳርድ ዲዛይኖችን አዘጋጅቶ የማቅረብ ወይም በማህበራቱ በራሳቸው ተዘጋጅተው የቀረቡትን ዲዛይኖችን በህንፃ ሹም አማካኝነት የማጸደቅና ሌሎች ድጋፎችን በማድረግ በተቀናጀ አግባብና በጸደቀው የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ስትራቴጂ መሰረት መፈጸማቸውን ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

(ሐ) ለተለያዩ የከተሞች ደረጃ እና የተለያዩ ለመሬት አጠቃቀም የሚሆኑ ሞዴል የግንባታ ዲዛይኖችን ከተሞች እንዲያዘጋጁ ለከተሞች ድጋፍ ያደርጋል፤

(መ) ቤቶች ተገንብተው እስከሚጠናቀቁ ድረስ ያለውን የግንባታ ሂደት ህንጻ ሹም እንዲከታተል የሚመራ አደረጃጀት ያዘጋጃል፤ቁጥጥር ያደርጋል።



Gumuz Regional State Administrative Council

#0647 P.010/023
22/06 2008 17:13

2. የክልሉ የዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

(ሀ) በክልሉ የሚዘጋጁ መመሪያዎችን፣ ማንዋሎችን፣ ቅጾችን፣ ወዘተ... በወቅቱ ለውጪ ጉዳይ ሚኒስትር መላክ፤

(ለ) በክልሉ የመኖሪያ ቤት ለመስራት በመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበራት የተደራጁ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን ዝርዝር ከውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በመቀበል ለክልሉ ኅብረት ስራ ማኅበራት ቢሮና ልሎች ባለድርሻ አካላት ያቀርባል፤

(ሐ) በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ለክልሉ ከሚሲዮኖች የሚላኩ የተሞሉ ቅጾችንና የማህበራት መመስረቻ ቃለ ጉባዔ፣ መተዳደሪያ ደንብና ሌሎች መረጃዎችን ለክልሉ ከተማ ልማትና ኮንስተራክሽን ቢሮ ፣ ለክልሉ ኅብረት ስራ ማኅበራት ቢሮና ልሎች ባለድርሻ አካላት ያቀርባል፤

(መ) ወደ ክልሉ የመጡ የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበራትን የምዝገባ ዕውቅና የሚገልጽ ደብዳቤ ከሚመለከታቸው የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃ የሥራ ክፍሎች ሲላክ ለሚሲዮኖች እንዲደርስ ለውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ማስተላለፍ፡፡

3. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተግባርና ኃላፊነት

(ሀ) በውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በግልም ሆነ በመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበር ተደራጅተው ለምዝገባ የሚቀርቡ ቤት ፈላጊዎች እንደአግባቡ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር/ከክልሉ የዲያስፖራ ጽህፈት ቤትና ከኅብረት ስራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ቢ.ሮ በሚደርሰው ዝርዝር መሠረት የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፤

(ለ) በማኅበሩ ስም የተከፈተው የሂሳብ እንቅስቃሴ በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብና በውሉ መሰረት እንዲንቀሳቀስ ያደርጋል፤

(መ) በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር / በክልሉ የዲያስፖራ ጽህፈት ቤት በሚቀርበው ጥያቄ መሠረት ለግል ተመዝጋቢዎች ገንዘብ ማስተላለፊያ የሚያገለግል የጡል ሂሳብ ይከፍታል፤

(ሠ) የግል ተመዝጋቢዎች የሚከፈትን የባንክ ሂሳብ በተመለከተ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር / ለክልሉ የዲያስፖራ ጽህፈት ቤት ወቅታዊ መረጃ ይሰጣል፤



#0647 P.011/023
22/06 2008 17:14

(ረ) በተመሳሳይ ሁኔታ ከክልሉ ከተማ ልማትና ኮንስተራክሽን ቢሮ በኩል ጥያቄ ሲቀርብለት ለመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበራት ለተደራጁ የዲያስፖራ አባላት ገንዘብ ማስተላለፊያ የሚያገለግል ሂሳብ ይከፍታል፡፡

**3. የክልሉ የኅብረት ስራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ቢሮ ተግባርና ኃላፊነቶች**

(ሀ) በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን እና ተመላሽ ዳያስፖራ በመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበር ተደራጅተው ለመመዝገብ የሚያስፈልጋቸውን የአደረጃጀት መመሪያዎችንና ቅጾችን ያሳውቃል፣ያደራጃል፤ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር /ለክልሉ የዲያስፖራ ጽህፈት ቤት እንደአስፈላጊነቱ ውክልና በመስጠት እንዲደራጁ ያደርጋል፤

(ለ) በውጭ ለሚኖሩ በመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበር አማካኝነት ለመደራጀት የሚያስፈልጋቸውን ዝርዝር መመሪያና ሞዴል ቅጾች በማዘጋጀት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር/ በክልሉ የዲያስፖራ ጽህፈት ቤት/ በኩል እንዲደርሳቸው ያደርጋል፤

(ሐ) ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልተው የቤት ፈላጊዎች ምዝገባ ለመጠቀም በውጭ የተደራጁ (ካሉ) ነባርና አዲስ የመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበራት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር/ከክልሉ የዲያስፖራ ጽህፈት ቤትና ከንግድ ባንክ ጋር በመተባበር የቁጠባ ሂሳብ እንዲከፈትላቸው ያደርጋል፤ የመኖሪያ ቤቱን የግንባታ ክፍያ 50 ፐርሰንት ያሟሉና ሌሎች ለምዝገባ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላታቸውን በማረጋገጥ የምዝገባ እውቅና ሰርቲፊኬት እንዲያገኙ ያደርጋል፤

(መ) ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር /ከክልሉ የዲያስፖራ ጽህፈት ቤት/ በተላከለት የአባላት ዝርዝርና በንግድ ባንክ መረጃ መሰረት ክፍያ ያጠናቀቁ የኅብረት ስራ ማኅበራትን የመኖሪያ ቤት ለመስራት በመረጡት ከተማ የምዝገባ እውቅና ሰርቲፊኬት እንዲያገኙ ያደርጋል፤

(ሠ) የተመዘገቡና ቅድመ ሁኔታዎችን ያሟሉ የመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበራት የቦታ ዝግጅትና ግንባታ ፈቃድ እንዲያገኙ ለከተማው አስተዳደር/ማዘጋጃ ቤት በማቅረብ እንዲፈቀድ ያደርጋል፤

(ረ) ነዋሪነታቸዉ በውጭ አገር ቢሆንም በምዝገባው ወቅት በአካል አገር ቤት የሚገኙ የመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበር አባላትን በተመለከተ በውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሳብ ከፍተው በአካል ቀርበው እንዲመዘገቡ ያደርጋል፤

(ሰ) በኢፌዲሪ ሚሲዮኖች ተመድበው የሚያገለግሉ ዲፕሎማቶችና ሎካል ሰራተኞች በመኖሪያ ቤት ሕብረት ሥራ ማኅበራት የተደራጁ አባላት ዝርዝር መረጃ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር/ በክልሉ የዲያስፖራ ጽህፈት ቤት/ በተላከለት እና በኢትዮጵያ



#0647 P.012/023
22/06 2008 17:14

ንግድ ባንክ መረጃ መሠረት የግንባታውን ወጪ 50 በመቶ ያጠናቀቁ የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበራት የምዝገባ እውቅና ሰርቲፊኬትእንዲያገኙ ያደርጋል፤

(ሸ) በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ዲፕሎማቶችና ሎካል ስራተኞች ምዝገባ የፈጸሙባቸውን ቅጾች፣ የመተዳደሪያ ደንቦች፣ የአመራር ምርጫ ቃለ ጉባኤና ሌሎች መረጃዎችን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር /ከክልሉ የዲያስፖራ ጽህፈት ቤት/ ይረከባል፣ ያደራጃል፤

(ቀ) የቤቶች ግንባታ በውሉ መሠረት ሲጠናቀቅ ለማህበሩ አባላት በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ያስረክባል፤

(በ) ቤቶቹ ተገንብተው እስከሚጠናቀቁ ድረስ ያለውን የግንባታ ሂደት የሚከታተል/ የሚመራ አደረጃጀት ይፈጥራል፡፡

4. **የከተማው አስተዳደር/ማዘጋጃ ቤት ተግባርና ኃላፊነት**

(ሀ) በመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማህበር ተደራጅተው የምዝገባ ሰርተፊኬት ያገኙ ህብረት ሥራ ማኅበራት በአደራጁ አካል በሚቀርብ ጥያቄ አማካኝነት የመሬት ዝግጅት ያደርጋል፣ የግንባታ ፈቃድ ይሰጣል፣የቤቱን መስሪያ መሬት ከነማረጋገጫ ፕላኑ እና ሰነዱ ጋር በማዘጋጀት ለኅብረት ሥራ ማኅበሩ ይሰጣል፣ስለመስጠቱም ለአደራጅ መስሪያ ቤቱ ያሳውቃል፤

(ለ) ከመሰረተ ልማት ዘርጊ ተቋማት ጋር በመተባበር ለግንባታው የሚያሥፈልግ መሰረተ ልማት እንዲሟላ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

(መ) እንደ ከተሞች ባህሪ እና እንደ ማኅበራት ምርጫ ዲዛይን እንዲዘጋጅ ድጋፍ ይደረጋል ማህበራት ሲያቀርቡም ተከታትሎ ያስፈጽማል፤

(ሠ) የከተማው አስተዳደር/ማዘጋጃ ቤት ለአዲስም ሆነ ለነባር ማኅበራት የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የሚሰጠዉ በምደባ ስረዓት ሆኖ በሊዝ መነሻ ዋጋ ይሆናል፡፡

5. **የቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ ተግባርና ኃላፊነት**

(ሀ) በመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበር ተደራጅተውና እውቅና ተሰጥቷቸው ከሚመለከተው አደራጅ አካል በሚቀርበው ዝርዝር ዝግጅት የግንባታ የውል ስምምነት ይፈጽማል፤ በየደረጃው ግንባታቸው እንዲከናወን ያደርጋል፤ ግንባታቸው የተጠናቀቀውን ቤቶች ለሚመለከተው የኅብረት ስራ ማኅበራት ያስረክባል፤

(ለ) ለግንባታ የሚያስፈለገው በዝግ አካውንት የተቀመጠውን የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ገንዘብ ግንባታውን ለማስጀመር የሚያስፈልገውን እንዲሁም የግንባታ ሥራውን በየደረጃው ለማከናወንና ለማጠናቀቅ የሚያስችለውን ፋይናንስ በየጊዜው በሚቀርብ የግንባታ አፈጻጸም መሠረት ደረጃ በደረጃ እየታየ እንዲለቀቅለት ይጠይቃል፤

(ሐ) የኅብረት ሥራ ማኅበራቱ በተረከቡት መሬት ላይ በአግባቡና በዲዛይኑ መሠረት የሥራ ተቋራጮችን፣ አማካሪዎችንና ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በማሳተፍ የቤቶችን ግንባታ በተቀመጠው ስታንዳርድና ውል መሠረት በማከናወን የህብረት ስራ ማህበራት የሥራ ክፍል ያስረክባል፡፡



Benishangul Gumuz Regional State Administrative Council

#0647 P.013/023
22/08 2008 17:15

## አንቀጽ 11

## የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሳዊ ሪፐበሊክ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዚህን መመሪያ አተገባበር በተመለከተ በልዩ ልዩ አካላቱ በኩል የሚከተሉትን ተግባሪና ኃላፊነት ይኖረዋል

1) የዉጭ ሚሲዮኖች ተግባሪና ኃላፊነት

(ሀ) በግል ተመዝጋቢዎችና በመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበራት ለተደራጁ የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ማስፈጸሚያ በተዘጋጁ መመሪያዎች ላይ በሚሲዮኑ እንዲሁም በተወከሉባቸው አገሮች ለሚገኙ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላት ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ መስራት፤

(ለ) በግል ተመዝጋቢዎችና በመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበራት ፕሮግራም መመሪያው ላይ የተቀመጠውን የምዝገባ ቀናት፣ የምዝገባ ቦታና ተመዝጋቢዎች የሚጠበቅባቸውን መስፈርቶች እንዲያሟሉ በግልጽ የማስገንዘብ ስራ መስራት፣ አደረጃጀታቸውን በአግባቡ ማጠናቀቅ፤

(ሐ) በግል ተመዝጋቢዎችና ለመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበራት ፕሮግራም ተመዝጋቢዎች እንዲሞሉ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተላኩ ቅጾችን በበቂ ሁኔታ በማዘጋጀት ማስሞላት፤

(መ) በግል ተመዝጋቢዎችና በመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበራት ፕሮግራም የተመዘገቡትን የአባላት ዝርዝር እንዲሁም የተሞሉ ቅጾችንና ሌሎች ተፈላጊ መረጃዎችን እና አባላትን በጥንቃቄ በማደራጀት በዲፕሎማቲክ ፖውች በወቅቱ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል እንዲደርስ ማድረግ፤

(ሠ) ስለ መኖሪያ ቤት የኅብረት ስራ ማኅበር አደረጃጀትና አሰራር ከሚመለከተው የህብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃ የሥራ ክፍል በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል የሚላኩትን የተለያዩ ሰነዶች፣ ቅጾችና ውሎች በተገቢው መንገድ ለተጠቃሚዎች መድረሳቸውን ማረጋገጥ፤

(ረ) ቅሬታዎች፣ ጥያቄዎች እንዲሁም ማብራሪያ የሚያስፈልጉ ጉዳዮች ካጋጠሙ በወቅቱ ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳሬክቶሬት ጄኔራል ለዋናው መስሪያ ቤት ማቅረብ፤

(ሰ) በግል ተመዝጋቢዎችን በተመለከተ መደራጀት ባይጠበቅባቸውም ሚሲዮኑ ለአፈጻጸም አመች እንዲሆን ተመዝጋቢዎቹን በቡድን በመለየት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳሬክቶሬት ጄኔራል በሸኚ ደብዳቤ የቡድኑን አባላት ዝርዝር በማካተት መላክ፤



22/06 2008 17:15 #0647 P.014/023

(ሸ) በግል ተመዝጋቢዎችና የመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበራት ፕሮግራም የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ምዝገባ በጸደቀው መመሪያ መሠረት ብቻ መፈጸሙን ማረጋገጥ፣

(ቀ) በእያንዳንዱ አዲስ የመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበር የተሞሉ የአባላት ቅጾች፣ የተደራጁበት የመተዳደሪያ ደንብ፣ የአመራር አባላትን የመረጡበት የተፈረመ ቃለ-ጉባኤ፣ የፈለጉትን የቤት አይነት ከሚሲዮኑ የመሸኛ ደብዳቤ ጋር መላክ፤

(በ) በክልሉ ከተሞች አዲስ የመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበር አባላት ከ14 እና ከዚያ በላይ መሆናቸውን በማረጋገጥ ሚሲዮኑ ሞዴል የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራትን መተዳደሪያ ደንብ በማቅረብ እንዲሞሉት በቃለ-ጉባዔም የተደገፈ የአመራር አባላት መምረጥና ተፈራርሞ መላክ፡፡

2) **በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል**

(ሀ) አስፈላጊ መመሪያዎችን፣ ማንዋሎችን፣ ቅጾችን፣ ወዘተ... በወቅቱ ለሚሲዮኖች መላክ፤

(ለ) ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር በወቅቱ ለሚሲዮኖች እንዲደርሱ ማድረግ፣

(ሐ) ከሚሲዮኖች የሚላኩ የተሞሉ ቅጾችንና የማህበራት መመስረቻ ቃለ ጉባዔ፣ መተዳደሪያ ደንብና ሌሎች መረጃዎችን ለሚመለከታቸው የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃ የሥራ ክፍሎች መላክና ስለጉዳዩ ክትትል ማድረግ፤

(መ) የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበራትን የምዝገባ ዕውቅና የሚገልጽ ደብዳቤ ከሚመለከታቸው የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃ የሥራ ክፍሎች ሲላክ ለሚሲዮኖች ማስተላለፍ፤

(ሠ) ከሚሲዮኖች፣ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ከሚመለከተው የቁጠባ ቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ እና ከሚመለከታቸው የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃ የሥራ ክፍሎች ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችን በተመለከተ መከታተልና መረጃ መያዝ፤

(ረ) ሚሲዮኑ በላካቸው የግል ተመዝጋቢዎች ዝርዝር መሠረት የባንክ ሂሳብ እንዲከፈት ማድረግ፤

(ሰ) የግል ተመዝጋቢዎችን በተመለከተ ከመዝገባቸው በፊት የጋራ አካውንት በእያንዳንዱ ማኅበር ስም እየተመዘገበ እንዲከፈት ያደርጋል፤

(ሸ) የግል ተመዝጋቢዎችን በማኅበር እያደራጀ ከአስፈላጊ መረጃዎች ጋር ለምዝገባ ለማኅበራት ማደራጃ ይልካል፤

(ቀ) ተመላሽ ዳያስፖራ አባላትን በተመለከተ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መሥፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የምዝገባ የብቁነት ማስረጃ ይሰጣል፡፡

1. የተመላሽ ዳያስፖራው የጸና የፖስፖርት ቅጂ፤
2. ተመላሽ ዳያስፖራው የሌላ አገር ዜግነት ያገኙ ከሆነ የጸና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፤
3. የጋብቻ ማስረጃ ዋናውንና ቅጂውን፤
4. የተመላሽ ዳያስፖራው ሁለት ፖስፖርት መጠን ፎቶ ግራፍ፤
5. ለዚህ ጉዳይ የተዘጋጀ የምዝገባ ቅጽና ውል በወካዩ ሥም ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ፤
6. በመረጡት የመኖሪያ ቤት አይነት የግንባታውን ወጪ 50 በመቶ በውጭ ምንዛሪ ከፍለው በአገር ውስጥ በተከፈተው የባንክ አካውንት ገቢ ያደረጉበትን የክፍያ ደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡



#0647 P.015/023
22/06 2008 17:15

3) በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሰው ሀብት ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ጄኔራል

(ሀ) በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሚሲዮኖች ተመድበው እያገለገሉ የሚገኙ ዲፕሎማቶች እና ሎካል ሠራተኞች በመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበራት የምዝገባ ቅጽ፤የተደራጁበትን የመተዳደሪያ ደንብ፣ የአመራር አባላት የመረጡበትን የተፈረመ ቃለ ጉባኤ፣ የፈለጉትን የመኖሪያ ቤት ዓይነት እና የሚሲዮኑን ሸኚ ደብዳቤ ለሚመለከታቸው የህብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃ የሥራ ክፍሎች ያስተላልፋል፤

(ለ) በመኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማኅበራት የተደራጁ በኢፌዲሪ ሚሲዮኖች ተመድበው እያገለገሉ የሚገኙ ዲፕሎማቶችና ሎካል ሰራተኞች ምዝገባ በቅርበት በመሥራት ተከታትሎ ያስፈጽማል፤ ተፈላጊውን መረጃ ለዲፕሎማቱና ለሎካል ሠራተኛው በሚሲዮኖች አማካኝነት ያሳውቃል፤

(ሐ) አካውንት የሚከፈትላቸውን ዲፕሎማቶችና ሎካል ሠራተኞች አባላት ዝርዝር ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያስተላልፋል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

## አንቀጽ 12

## ስለውክልና

1) ማንኛውም በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የመኖሪያ ቤት ፈላጊ ለመመዝገብና ሌሎች ጉዳዮችን ለመከታተል በአካል መቅረብ ካልቻለ ተወካይ መወከል ይችላል፡፡ ሆኖም ግን አንድ ተወካይ ከአንድ በላይ ለሆኑ ዲያስፖራዎች በአንድና በተመሳሳይ ጊዜ ወኪል ሊሆን አይችልም፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰተረት የተወከለ ማንኛዉም ሰዉ የማኅበር አባልም ሆነ የግለሰብ ተመዝጋበውን ወክሎ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ በዚህ ማስፈጸሚያ መመሪያ የተደነገጉትን ጉዳዮች አክብሮ የመስራት ኃላፊነት አለበት፤

3) ተወካዩ የተሳሳቱ መረጃዎችን በማቅረብ ወካዩ ተጠቃሚ እንዲሆን ካደረገ እንደያልተገባ ጥቅም ተጋሪ ተቆጥሮ በህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 13

## የምዝገባ ጊዜ

የግል ተመዝጋቢዎች ሆነ የመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበራት የተደራጁ አባላት ምዝገባ ይህ መመሪያ ጸድቆ ስራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡



22/06 2008 17:16 #0647 P.016/023

## አንቀጽ 14

## የሂሳብ እንቅስቃሴና የገንዘብ ዝውውር ሁኔታ

1) የመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበራት የሂሳብ እንቅስቃሴ ሁኔታ በመተዳደሪያ ደንቡና ለመኖሪያ ቤት በዝግ ሂሳብ የተቀመጠ ገንዘብ የኅብረት ስራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ቢሮ የሥራ ክፍል በተወካይ የሥራ አመራር ወይም በዋና የሥራ አመራር አማካኝነት እንዲንቀሳቀስ ሲፈቅድና ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሲጽፍ የሚንቀሳቀስ ይሆናል፤
2) በግል ተመዝጋቢዎች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አማካይነት ከሚከፈትላቸው የግል አካውንት ላይ ወደ ተደራጁበት ማኅበር ሂሳብ እንዲዘዋወር ከማኅበራት ማደራጃ በሚደርሰው ትዕዛዝ መሠረት ይህንኑ በመፈጸም ለማኅበራት ማደራጃ ያሳውቃል፡፡

## አንቀጽ 15

## የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ክትትል

1) በመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማህበር ተደራጅተው የተመዘገቡ አባላት እንዲሁም ተመሳሳይ በግል ተመዝግበው በመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበር ቤት ለመስራት የሚፈልጉ አባላት የቤት ግንባታ በመረጡትና በተዋዋሉት ስራ ተቋራጭ አማካኝነት ሊገነቡ ይችላሉ፤
2) የቤቶች ግንባታ የጥራት ቁጥጥር በክልሉ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ እና በመዋቅሩ በተዋረድ እስከታችኛዉ ድረስ ባለዉ (ዞን መምሪያዎች፣ከተማ አስተዳደር፣ማዘጋጃ ቤቶች) አማካኝነት ይሆናል፤
3) የግንባታውን ሂደት፣ የክፍያ አለቃቀቅ እና የጥራት ቁጥጥር ሥርዓት የሚደግፍ አደረጃጀት ይፈጠራል፣
4) በማህበር የሚገነቡ ቤቶች ርክክብ የሚፈጸመዉ የቤቶቹ ግንታ መቶ በመቶ መጠናቀቁ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡

## አንቀጽ 16

## የመኖሪያ ቤት ርክክብና ቅደም ተከተል አወሳሰን

1) ከዚህ በፊት በማኅበር ተደራጅተው የነበሩ በውጭ አገር ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በድጋሚ በዚህ መመሪያ መስፈርቱን አሟልተው ከተመዘገቡ ከአዲስ ተመዝጋቢ ማህበራት ቅድሚያ መብት ይኖራቸዋል፤
2) በማህበር የተደራጁ አባላት የመኖሪያ ቤት ርክክብን በተመለከተ ማህበሩ ግንባታውን ከሚያከናውነው አካል ጋር በገቡት ስምምነት መሠረት የሚፈጸም ሲሆን ለእያንዳንዱ የማህበር አባል የቤት ርክክብ የሚፈጸመው ግን በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አማካኝነት ይሆናል፤
3) በግል የተመዘገቡ ቤት የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎችን በተመለከተ የቤት ግንባታ የሚካሄድላቸው በጋራ ሲሆን የመረጡትን ቤት መሠረት በማድረግ በዕጣ እንዲከፋፈሉ ይደረጋል፤
4) የመጀመሪያውን ፎርማሊቲ አሟልተው 50 በመቶ ክፍያ ያጠናቀቁና እውቅና ያገኙ ማበራት ቁጥር ለግንባታ ከተዘጋጀው መሬት በላይ ከሆነ የቦታ አሰጣጡ የማኅበራቱ ተወካዮች በተገኙበት በዕጣ እንዲወሰን ይደረጋል፤
5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት በዕጣ መሬት የደረሳቸው ማኅበራት መሬቱ በተለያዩ የከተማው አካባቢዎች የሚገኝ ከሆነ ምርጫቸው በዕጣ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 17
## ከፕሮግራሙ ስለመሰረዝ

1) በግል ተመዝጋቢዎችም ሆነ በማኅበር የተደራጁ ተመዝጋቢው የምዝገባ መመሪያውን መስፈርቶች ሳያሟላ የተመዘገበ እንደሆነ ከምዝገባ ፕሮግራሙ ከመሰረዙ በተጨማሪ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፤
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም ከማኅበሩ አባላት ውስጥ አንዱ ወይም የተወሰኑት አባላት መስፈርቶችን የማያሟሉ ከሆነ በግል ተጠያቂ ሆነው ማኅበሩ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የሚቀጥል ይሆናል።

## አንቀጽ 18
## ቁጠባው ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ

በግል ተመዝጋቢዎችም ሆነ ከመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበራት መኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ምዝገባ ተሰርዞ ገንዘቡ እንዲመለስ የተወሰነ ተጠቃሚ ግለሰብ ወይም ማኅበር የሚመለሰው ገንዘብ በወቅቱ ምንዛሪ በኢትዮጵያ ብር ሆኖ በቁጠባ ውሉና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ነው።

## አንቀጽ 19
## ክልከላ

1) በክልሉ በጸደቀው የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበራት የአደረጃጀት መመሪያ የተቀመጡ ክልከላዎች በሙሉ በዚህ ማስፈጸሚያ መመሪያ ተፈጻሚነት አላቸው።
2) በዚህ መመሪያ ከተቀመጠው መስፈርት ውጭ መመዝገብም ሆነ እንዲመዘገብ ማድረግ የተከለከለ ነው።

## አንቀጽ 20
## ቅጣት

በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን የምዝገባ መስፈርቶች ሳያሟላ የተመዘገበ እና ክልከላዎችን የተላለፈ፣ ለመመዝገብ የሞከረ ወይም ሀሰተኛ መረጃ በማቅረብ የተመዘገበ ማንኛውም ተመዝጋቢም ሆነ የተመዝጋቢ ተወካይ አግባብ ባለው የፍትሐ ብሔር ሕግ ተጠያቂነት የተጠበቀ ሆኖ በወንጀል ህጉ ተጠያቂ ይሆናል።

## አንቀጽ 21
## የመተባበር ግዴታ

ማንኛዉም ሰዉ ወይም በህግ የስዉነት ስልጣን የተሰጠዉ አካል ይህን መመሪያ የመፈፀምና የመተባበር ግዴታ አለበት።

## አንቀጽ 22
## ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸዉ መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።



Benishangul Gumuz Regional State Administrative Council

#0647 P.018/023
22/06 2008 17:16

### አንቀጽ 23

### መመሪያውን የማሻሻል ስልጣን

ይህን መመሪያ ማሻሻል ሲያስፈልግ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሊያሻሽለው ይችላል።

### አንቀጽ 24

### መመሪያዉ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ከሚያዝያ 08 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አህመድ ናስር አህመድ**

**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት**

**ርዕሰ-መስተዳድር**



#0647 P.019/023
22/06 2008 17:17

ቅጽ 01

ፎቶ

## አባሪ አንድ

በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት በአፓርትመንት ወይም ቪላ በግል የመኖሪያ ቤት ልማት ፕሮግራም ላይ ለመመዝገብ የቤት ፍላጎት መግለጫ ቅጽ፣

1. **የአመልካች ሁኔታ፣**

1.1. ስም -------------------- የአባት ስም -------------------የአያት ስም ---------------------
ፆታ --------------- ዕድሜ------------------ ብሔር--------------------------
ዜግነት--------------------- የፓስፖርት ቁጥር-------------------------------

1.2 **የአመልካች እናት ስም** ----------------------- የእናት አባት ስም ------------------------------
የእናት አያት ስም -----------------------------------

1.3 **የመኖሪያ አድራሻ**

- አገር-----------------------------------ከተማ-----------------------------------
- ፖ.ሳ.ቁ.------------------------------ ፋክስ ቁጥር--------------------------
- ስልክ ቁጥር-----------------------------ኢሜል --------------------------

1.4 **የትዳር ሁኔታ**
ያገባ/ች ☐ ያላገባ/ች ☐ በፍቺ የተለየ/ች ☐ በሞት የተለየ/ች ☐

1.5 ያገባ/ች ከሆነ የትዳር ጓደኛ ስም---------------የአባት ስም---------------- የአያት ስም -------------------

2. **የሚፈልጉት የቤት አይነት**

2.1. አፓርትመንት/ የጋራ ህንጻ (ፎቅ)ከሆነ ፤
ባለ 2 መኝታ ☐ ባለ 3 መኝታ ☐ ባለ 4 መኝታ ☐

2.2 ቪላ ከሆነ፣

ባለ 3 መኝታ ☐ ባለ 4 መኝታ ☐

3. **የገቢ ሁኔታ**

3.1. የአመልካች ወርሃዊ የገቢ መጠን በብር -------------------------- ምንጭ ------------------
3.2. የትዳር ጓደኛ የገቢ መጠን በብር ---------------------- ምንጭ ---------------------------
3.3. ጠቅላላ የገቢ መጠን በአኃዝ ------------ /በፊደል-----------------------------------

4. **የተወካይ መረጃ፤**

4.1 የተወካዩ ስም ከነአያት-------------------------------------------------------------

4.2. የተወካዩ የመኖሪያ አድራሻ ፡-
- ክልል-------------------------ከተማ-----------------------------------
- ዞን/ክ/ከተማ---------------------------ወረዳ -------------------------
- ቀበሌ --------------------------የቤት ቁጥር ---------------------------
- የቤት ስልክ ቁጥር ------------------የሞባይል ስልክ ቁጥር ---------------------

5. **ለምዝገባ የሚያስፈልግ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያስቀመጠው ገንዘብ**

5.1 በቅድሚያ በልዩ ዝግ ሂሳብ ያስቀመጠው ዝቅተኛ መጠን ብር በአኃዝ ------------------
/በፊደል-------------------------------------------------------------------------------/
5.2 የዝግ ሂሳብ የቁጠባ ደብተር ቁጥር ---------------------------------------- ቅርንጫፍ ---------------



#0647 P.020/023
22/06 2008 17:17

6. **ሂሳብ የሚከፍትበትና የቤቱን ዋጋ ክፍያ የሚፈጸምበት አማራጭ መንገድ፡-**

6.1. የክፍያ አፈጻጸም በአንድ ጊዜ (100%) ☐ በሁለት ጊዜ (50%) ☐

7. **እኔ ስሜ ከላይ የተገለጸው አመልካች**

7.1 ቀደም ሲል በመንግስት በተዘረጉት በማናቸውም የቤት ልማት ፕሮግራሞች ያልተመዘገብኩ መሆኑን፣

7.2 ግንባታ እንዲካሄድልኝ በመረጥኩት ከተማ ውስጥ በራሴ ወይም በትዳር ጓደኛዬ ስም የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት ወይም የቤት መስሪያ ቦታ የሌለኝ እና ከዚህ በፊትም የነበረኝን በሽያጭ ወይም በስጦታ ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፍኩ እና በመንግስት በተዘረጉት የቤት ልማት ፕሮግራሞች ከዚህ በፊት ተጠቃሚ ያልሆንኩኝ መሆኑን፣

7.3 ለምዝገባ ብቁ የሚያደርገኝ የቤቱን ግንባታ 50 ፐርሰንት በምዝገባ ወቅት በውጭ ምንዛሪ በዝግ ሂሳብ ማስቀመጤን፣ ቀሪውን 50 በመቶ መሬት ተዘጋጅቶ የግንባታ ፍቃድ ሲሠጥ የማስቀምጥ መሆኑን፣

7.4 በምረከበው ቤት በጋራ ህንፃ ህግ መሠረት ለመተዳደር ፈቃደኛ መሆኔን፣

7.5 በዚህ ማመልከቻ ቅጽ የሞላሁትና የሰጠሁት ማረጋገጫ ሀሰተኛ ሆኖ ቢገኝ የምዝገባው ውል የሚፈርስ መሆኑንና ቤቱን ለሚመለከተው ለማስረከብ ወይም በከፍተኛ የሊዝ ዋጋ ታስቦ ከነቅጣቱ ለመክፈል የምስማማ መሆኑን፣

7.6 ወደፊት የሚጠየቁ መረጃዎችን ለምሳሌ የጣት አሻራና ሌሎች መረጃዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኔን እንዲሁም፣

7.7 ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ተጠሪ የቤቱን ጉዳይ ተከታትለው እንዲያስፈጽሙ የወከልኳቸውና የሞላሁት መረጃ ሀሰት ሆኖ ቢገኝ በህጉ መሠረት ተጠያቂ እንደምሆን በመስማማት ይህን ቅጽ የሞላሁ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የአመልካች ሙሉ ስም-----------------------------------

ፊርማ -------------------------------

ቀን --------------------------------

<u>ማሳሰቢያ፡-</u> ይህ ቅጽ በእያንዳንዱ በግል ተመዝጋቢዎች ወይም ወኪል አማካኝነት ተሞልቶ የሚቀርብ ነው፡፡



22/06 2008 17:17 #0647 P.021/023

ቅጽ 02

ፎቶ

<u>አባሪ ሁለት</u>

በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን እንዲሁም ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት በመኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበራት ለማደራጀት የአባልነት ማመልከቻ ቅጽ

1. የህብረት ስራ ማህበሩ መጠሪያ------------------------------------------------------------------የመኖሪያቤት ኃ/የተ/የህ/ስ/ማ
2. የአመልካች ሁኔታ፣
   2.1. ስም ---------------- የአባት ስም ----------------የአያት ስም ---------------------
   ፆታ -------- ዕድሜ----------- ብሔር-------------- ዜግነት----------- የፓስፖርት ቁጥር------------
   2.2 የአመልካች እናት ስም ------------------------ የእናት አባት ስም -------------------------------
   የእናት አያት ስም---------------------------------------
   2.3. የመኖሪያ አድራሻ
      2.3.1 አገር---------------------------------------
      2.3.2 ከተማ---------------------------------------
   2.4 የትዳር ሁኔታ
   ያገባ/ች ☐ ያላገባ/ች ☐ በፍቺ የተለየ/ች ☐ በሞት የተለየ/ች ☐
   2.5. ያገባ/ች ከሆነ የትዳር ጓደኛ ስም -----------------የአባት ስም--------------የአያት ስም---------------------
3. የሚፈልጉት የቤት አይነትና የክፍል ብዛት
   3.1 አፓርትመንት/ የጋራ ህንጻ (ፎቅ)ከሆነ፤
   ባለ 2 መኝታ ☐ ባለ 3 መኝታ ☐ ባለ 4 መኝታ ☐
   3.2 ቪላ ከሆነ፣
   ባለ 3 መኝታ ☐ ባለ 4 መኝታ ☐
4. የተወካይ መረጃ፤
   4.1 የተወካዩ ስም ከነአያት-----------------------------------------------------------------
   4.2 የተወካዩ የመኖሪያ አድራሻ ፡-
   - ክልል---------------------------ከተማ-----------------------------------------
   - ዞን/ክ/ከተማ-------------------------------ወረዳ ---------------------------
   - ቀበሌ ---------------------------የቤት ቁጥር ---------------------------
   - የቤት ስልክ ቁጥር ---------------------የሞባይል ስልክ ቁጥር ----------------------



#0647 P.022/023
22/06 2008 17:17

5 እኔ ስሜ ከላይ የተገለጸው አመልካች

5.1 ቀደም ሲል በመንግስት በተዘረጉት በማናቸውም የቤት ልማት ፕሮግራሞች ያልተመዘገብኩ መሆኑን፣

5.2 ግንባታ እንዲካሄድልኝ በመረጥኩት ከተማ ውስጥ በራሴ ወይም በትዳር ጓደኛዬ ስም የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት ወይም የቤት መስሪያ ቦታ የሌለኝ እና ከዚህ በፊትም የነበረኝን በሽያጭ ወይም በስጦታ ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፍኩ እና በቤት ልማት ፕሮግራም ከዚህ በፊት ተጠቃሚ ያልሆንኩኝ መሆኑን፣

5.3 ለምዝገባ ብቁ የሚያደርገኝ የቤቱን ግንባታ 50 ፐርሰንት በምዝገባ ወቅት በውጭ ምንዛሪ በዝግ ሂሳብ ያስቀመጥኩ መሆኑን እና ቀሪውን 50 በመቶ መሬት ተዘጋጅቶ የግንባታ ፍቃድ ሲሰጥ የማስቀምጥ መሆኔን፣

5.4 በምረከበው ቤት በጋራ ህንፃ ህግ መሠረት ለመተዳደር ፈቃደኛ መሆኔን፣

5.5 በዚህ ማመልከቻ ቅጽ የሞላሁትና የሰጠሁት ማረጋገጫ ሀሰተኛ ሆኖ ቢገኝ የምዝገባው ውል የሚፈርስ መሆኑንና ቤቱን ለሚመለከተው ለማስረከብ ወይም በከፍተኛ የሊዝ ዋጋ ታስቦ ከነቅጣቱ ለመክፈል የምስማማ መሆኑን፣

5.6 ወደፊት የሚጠየቁ መረጃዎችን ለምሳሌ የጣት አሻራና ሌሎች መረጃዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኔን እንዲሁም

5.7 በተ.ቁ 1 ላይ በተገለጸው የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ስም ከሌሎች የማህበሩ አባላት ጋር በፈቃደኝነት ለመደራጀትና የመኖሪያ ቤት ለመስራት የሚያስፈልገውን ቅድመ ሁኔታና መስፈርቶች በአዋጁና በመመሪያው መሰረት ያማላሁ በመሆኑ የህብረት ስራ ማህበሩ በአባልነት እንዲቀበለኝና ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ተጠሪ የቤቱን ጉዳይ ተከታትለው እንዲያስፈጽሙ የወከልኳቸውና የሞላሁት መረጃ ሀሰት ሆኖ ቢገኝ በህጉ መሠረት ተጠያቂ እንደምሆን በመስማማት ይህን ቅጽ የሞላሁ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የህ/ስ/ማ/አባሉ ሙሉ ስም-----------------------------------

ፊርማ --------------------------------

ቀን ----------------------------------

ማሳሰቢያ፡- ይህ ቅጽ በእያንዳንዱ የህ/ስ/ማህበሩ አባል ወይም ወኪል አማካኝነት ተሞልቶ የሚቀርብ ነው



22/06 2008 17:18 #0647 P.023/023